# ***የአገራችን ተቃዋሚዎች የፖለቲካ ተግባራቸውን እየተወጡ ይሆን?***

***በሰንታየሁ ግርማ 12-18-14***

***(sintayehuGirma76@gmail.com)***

የፖለቲካ ሳይንስ ባለሞያዎች፣ ፓርቲዎች በተለይም ተቃዋሚዎች የዲሞክራሲ ዋነኛ አካል ናቸው ይላሉ፡፡ ኢንለሰኮ እና ሣደራጋይ የተባሉ ተንታኞች "ተቋማዊ ተቃዋሚ መኖር አለመኖር የስርዓቱ ዲሞክራሲ መሆን ያለመሆን ማሣያ ነው" ይላሉ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከናወኗቸው ተግባራት በ2 ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ፡- አጠቃላይ እና ዝርዝር ተግባራት፣

## ***አጠቃላይ ተግባራት***

ፓርቲ እና የፓርቲ ስርዓት ዋነኛ ጠቀሜታ አንድ ስርዓት ባህሪ አስቀድሞ በማጠበቅ እና ሰላማዊ ተከታታይ በሆነ ሜሉኩ እንዲፈፀም ማድረግ ነው፡፡ ፓርቲዎች ሰላማዊ የመንግሥት ሽግግር እንዲኖር ያስችላሉ፡፡ ፓርቲዎች ከሌሉ ሁሉም በየግሉ በየፊናው እየተንቀሳቀሰ ሥልጣን ለማያዝ ይጥራል፡፡ ሽግግሩም ሰላማዊ አይሆንም፡፡ ፓርቲዎች ግን ህ/ሰቡ መደራጀት እንዳለበት በማስተማር ተመሣሣይ ሃሣብና ፍላጎት ያላቸው በጋራ እንዲሰባሰቡ ያስችላሉ፡፡ የፖርቲዎች ግብ የፖለቲካ ሥልጣን በማያዝ ህዝቡን ማገልገል ነው፡፡ ሥልጣን ለማያዝ ደግሞ በግልጽ የሚታወቅ ራዕይ፣ ፕሮግራሞች ሊኖራቸው ገባል፡፡ ማህበራዊ መሠረታቸውን በግልጽ በማየት የተነተነ ሀሣብ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ግልፅ ራዕይ ከሌላቸው አባል ለማሰባሰብ ይቸገራሉ፡፡ የጋራ (ምኞት) ከሌላቸው እና በአባሎቻቸው ካልተያዘ በጋራ ከማለፍ ይልቅ ማታረክ፣ማካፋፈል ማለያቸው ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም ማጠበቅ እና ማከበር የሚያምኑባቸው እና በጥብቅ የሚታገብሯቸው መርሆዎች መኖር አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ ፓርቲዎች የህ/ሰቡን ፖለቲካም ተሳትፎ መዋቅራዊ ሜልክ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ አጠቃላይ የፓርቲ ተግባራት ይባላሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት የሀገራችን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ስንመዘናቸው አጠቃላይ የፖለቲካ ተግባራትን እየተወጡ አይደለም፡፡ የሚጨረሻ ዓላማቸው በማንኛውም መንገድ ሥልጣን ማያዝ ነው፡፡ ሕጋዊ እና ሕገወጥ ተግባራት በመቀላቀል በአቋራጭ ሥልጣን ለማያዝ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የጋራ ራዕይ ስለሌላቸው ብዙ አባላት ማሰባሰብ አልቻሉም፡፡ የሚጋሩት የጋራ ራዕይ ባለመኖሩ መርህም የሌላቸው በመሆኑ እርስ በርሳቸው በፓርቲ ስያሜ ሳይቀር ሲነታረኩ ይኖራሉ፡፡ "አ" የሚለው ፊደል አማራን "ግ" የሚለው ቃል ኢህአዴግን ያስታውሰናል እስከማለት ይደርሳሉ፡፡ አንዱ አመራር ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት "አሃዳዊ" ነው ሲል ሌላው ደግሞ "በጂኦግራፊ" ላይ የተመሠረተ ፌዴራሊዝም ነው ይላሉ፡፡ በመርህ ተለያይተህ በፓርቲ ማሰባሰብ ደግሞ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በገንዘብ ያዥ፣በመዝገብ ቤት ሠራተኛ ቅጥር ሲነታረኩ ይኖራሉ፡፡ ለብሔራዊ ጥቅም መቆም ይሳናቸዋል (ለምሣሌ ኢትዮጵያ በአልሸባብ ያካሄዳቸውን) ዘመቻ ተቃውመው ነበር፡፡ በስንት

ልፋት የመጣውን የአበባ ኢንቨስትመንት ከርዕዮተ አለማቸው በሚቃረን መልኩ ይቃወሙታል፡፡ በአጠቃላይ ሁሉንም በጭፍን በመቃወም እነሱ ሥልጣን በማንኛውም መንገድ ለመያዝ የሚጥሩ በመሆናቸው አጠቃላይ የፓርቲ ተግባራትን እያከናወኑ አይደለም፡፡

ፓርቲዎች ከአጠቃላይ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

## 1. ሚሌማ ተግባር

ፓርቲዎች የነገው ፕሬዘዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስቴር የሚወጡባቸው ናቸው፡፡ ይህንን ለመወጣት የፓርቲያቸውን የውስጥ አሰራር ዴሞክራሲዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ የፓርቲ መሪዎች በነፃና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በአባሎቻቸው የሚመረጡ መሆን አለባቸው፡፡ መሣዝ

ኛውን ለሚያሚኢ ለማንኛውም ዜጋ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ በሀገራችን ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በስርዓቱ ላይ ባላቸው ጭፍን ጥላቻ የተሰባሰቡ፣ በወንዝ ልጅነት እና በጥቅማ ጥቅም የተሳሳቡ ናቸው፡፡ በብዙሃን ውሣኔ የማያምኑ እና የሚያገዙ ናቸው፡፡ የዴሞክራሲ ጭላንጭል እንኳን የማይታይባቸው ናቸው፡፡ አንድነት በተባለ ፓርቲ ወስጥ የፓርቲው አመራር ወይይት ሲያካሂዱ "አንተ ስለቴያትር እንጂ ስለ ፖለቲካ አታውቅም" ሲሉ በቴሌቪዥን ታይተዋል፡፡ እነዚህ የራሳቸውን ሰዎች እንዲህ ያሉ አብዛኛው አርሶ አደር በሆነበት እና ቀላል ያልተማረ የህብረተሰብ ክፍል ባለበት ሀገር ስልጣን ይዘው አርሶ አደሩ ባለጉዳይ ሆኖ ቢመጣ "አንተ ምንም ስለማታውቅ እኔ የምለውን ብቻ አዳምጥ" ሊሉ ነው? የሞራል፡ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ሰው ለመሆን የግድ በፖለቲካ ሳይንስ ወይንም በሕግ መመረቅ የግድ አይደለም፡፡

በወስጣቸው ቅንጣት ያህል የዴሞክራሲ አሠራር የሌላቸውም ናቸው፡፡ በምርጫ ስነ-ምግባር "ከእከሌ ጋር እወያያለሁ ከእከሌ ጋር አልወያይም" ማለት ታይቷል፡፡ በመጀመሪያ በወይይት ችግርን መፍታት የሰለጠነ የዴሞክራሲ ባህል ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርዓት ማኅቸውም ልዩነት ሊገለጽ የሚችለው እና የሚፈታው በወይይት ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ በጀርመን ሀገር የአርያንስ ዘር ራሱን ምርጥ ዘር ነኝ ብሎ የሚያምን በመሆኑና ይህንንም ህዝቡ ስለሚቀበለው እስከ አሁን በጀርመን ፓርላማ /ቡንደስታ/ መቀመጫ ማግኘት አልቻለም፡፡ እነዚህ ኃይሎች ስልጣን ላይ ቢወጡ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም፡፡ ከኢህአዴግ እንጂ ከኢዴፓ ወዘተ... አልወያይም፣ እኔን ከሚመስሉ እና የእኔ ሀሳብ ሁልጊዜ ትክክል ነው ብሎ ከሚያምን ጋር ብቻ መሆን አለበት ነው መልዕክቱ፡፡ ነገሩ በእኔ ሰሪ ልክ የተሰፋውን መልበስ አለብህ፡ የእኔን መዝሙር መዘመር አለብህ፣ እኔ ነኝ አዋቂ እኔ የምለውን ስማ ማለት ነው፡፡ ይህ የዴሞክራሲ መገለጫ አይደለም፤ ዴሞክራሲ ማለት ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ እና በወይይት መፍታት ነው፡፡ በሚያስማማ ጉዳይ ላይ በጋራ መስራት፣ በማያስማማው ጉዳዮች ላይ ልዩነትን ማክበር ነው፡፡

ማቻቻል የዴሞክራሲ ባህል ምሰሶ ነው፡፡ ለዴሞክራሲ ግንባታ ሁሉንም በጭፍን መቃወም አይገባም፡፡ ተቃዋሚዎች ኃላፊነት ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው ተቃዋሚ በፕሪንት እና ብሮድካስት ሚዲያ ትንሹንም ትልቁንም እያንጠለጠለ የሚሄድ መሆን የለበትም፡፡ ስሜታዊ በመሆን በየጋዜጣው አንዱን ማህበረሰብ ከአንዱ ማህበረሰብ ሚጋጭ፣በወይይት እና በክርክር ወቅት መጥፎ ቃላቶችን ማጠቀም፣ የታማኝ ተቃዋሚ መገለጫ በፍፁም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመንግሥት ፖሊሲም ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ ለማስለወጥ አያስችልም፡፡ ተቃዋሚዎች ሚኒስትሮችንና የገዥው ፓርቲ አመራሮችን በማስመን፣ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ በፓርላማ በትብብር መሥራት ለሀገር የሚጠቅም ውሣኔ እንዲተላለፍ ለማድረግ አያስችላቸውም፡፡ ይህ ሲባል ግን ሰላማዊ ወይይት እና በእውነታ እና በሚጃ ላይ የተመሠረተ ትችት ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቁልፍ መሆኑ ማዝንጋት የለበትም፡፡ ለሁሉም ፓርቲዎች ስልጣን ማያዝ ብቸኛ ግብ መሆን የለበትም፡፡ ህዝብን በስልጣን ማገልገል እንጂ፡፡ ስልጣን የኢትዮጵያን ህዝብ ለማገልገል አንድ ግብ እንጂ ስልጣን ማያዝ ብቸኛ ግብ ተብሎ ከተያዘ ህዝብን በስሜት በመቀስቀስ ወደ ሁከት ማምራት ይመጣል፡፡ ስለዚህ ስልጣን በማንኛወም መንገድ የማያዝ ስግብግብነት የስልጡን ፖለቲካዊ ፓርቲ ባህሪ አይደለም፡፡

## 2. ፓርቲዎች በምርጫ በመወዳደር ምርጫ ፉክክር ያለበት እንዲሆን ያደርጋል

ፓርቲዎች በምርጫ በመወዳደር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲጎለብት የደርጋሉ፡፡ በሆነው ባልሆነው ከምርጫ ራሳቸውን ማግለል የለባቸውም፡፡ የዳበረ ዴሞክራሲ በ1 ጀምበር የሚነባ ስርዓት አይደለም፡፡ ምዕራባወያን የዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት 200 ዓመታት ፈጅቶባቸዋል፡፡ በምርጫ እየተወዳደሩ ችግሮች ካሉ በተቀማጠው ስርዓት ለመፍታት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡ በትንሹም በትልቁም ማኩረፍ ጠቃሚ አይደለም፡፡ ሕጋዊ ተቋማት የሚሰጡትን ውሣኔ መቀበል ይገባል፡፡ ለመካራከር ከተፈለገ በአሜሪካ በፕሬዝዳንት ቡሽና አልጎር መካከል የሚጨፈሻወን የምርጫ ውጤት የተቀበሉት በፍርድ ቤት ውሣኔ ነው፡፡ ተቃዋሚዎችባለፈው የአዲስ አበባ ማስተዳድር ባለሚረከብ እና ፓርላማ ባለመግባት ታሪካዊ ስህተት ሰርተዋል፡፡ ከዚያ በኃላ ለእነሱ ድምፅ የሰጠው ሰው አሜኔታ አይኖረወም፡፡ በእኔ ግምት ተቃዋሚዎች እርስ በእርሳቸው በመባላት ለገዢው ፓርቲ ምቹ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡ በጃፓን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በፓለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ምክንያቶች ህዝቦቹ ለብዙ አስርት ዓመታት ይሁንታቸወን ለ1 ፓርቲ ሰጥተዋል፡፡ የእኛ ተቃዋሚዎች በተጻፉ መርሆዎች አለመመራት፣ ግልጽ ፖሊሲና ፕሮግራም አለመኖር፣ የወስጥ ችግሮቻቸወን በዴሞክራሲ አለመፍታት፣ እርስ በእርሳቸው አለመወያየት፣ በየኤምባሲው በመሄድ በማለመን የሃገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ ለማስጠት መማከር ወዘተ... ላይ ማስሚራታቸው ህዝቡ አሜኔታ እንዲያጣባቸው ከማድረጉም በላይ በብዛት አባሎች ለማፍራት ስለቸገራቸው በምርጫ ብቁ ተወዳዳሪ አይደሉም፡፡

በሃገራችንም የዴሞ ክራሲ መሠረት እየተጣለ ነው፡፡ "በመጀመሪያ ሀገራዊ ምርጫ ከ5 እስከ 97 የምርጫ መቀመጫዎች ኢህአዴግ 480 (89.4) የፓርላማ መቀመጫዎች ሲያሸንፍ፣ አጋር ድርጅቶች 46 መቀመጫዎች 8 የግል ተወዳዳሪዎች አሸንፈው ነበር፡፡ በ2ኛ ሃገራዊ ምርጫ ደግሞ ኢህአዴግ 481 (97.93 በመቶ) መቀመጫዎች ሲያገኝ ተቃዋሚዎች ከበፊቱ በተሻለ 53 መቀመጫዎች (20 በመቶ) ሲያሸንፉ 13 መቀመጫዎች በግል ተወዳዳሪዎች ተይዘው ነበር፡፡ በእነዚህ ጊዜ የአናሳ ብሔሮች ወክልና ለሚጋገጥ የፓርላማ መቀመጫ ወደ 547 አድጎ ነበር፡፡ ከፌደራል ፓርላማ በተጨሪ በደቡብ ብሔረሰቦች ተቃዋሚዎች 10 በመቶ፣ በአዲስ አበባ ማስተዳደር ደግሞ 25 በመቶ መቀመጫዎች አግኝተው ነበር፡፡"

በ3ኛው እና በ4ኛው የሃገራዊ ምርጫ የአለምን ህዝብ ባስደመመ ሜኩ ለምርጫ ከተመዘገበው ህዝብ ወስጥ 90 በመቶ በምርጫው ወቅት ድምጹን ሰጥቶ ነበር፡፡ በዳበረ የዴሞክራሲ ስርዓት ባለባቸው ሃገሮች እንኳን ይህንን ያህል ህዝብ አይወጣም፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ማሪጥ ካለበት ህዝብ እስከ 50 በመቶ የሚምርጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ተቃዋሚዎች ከአዲስ አበባ ማስተዳደር መቀመጫ ከ138 ወስጥ 137 አግኝተው ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ዴሞክራሲው ምን ያህል እየጎለበተ መሄዱን የሚያሳይ በመሆኑ ተቃዋሚዎች በአግባቡ ቢጠቀሙበት ኖሮ የሚያሰኝ ነው፡፡

## 3.ጥቅሞችን ማጣጣም

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ ጥቅሞችንና ሃሳቦችን ለማጣጣም ያስችላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ግለሰብ የተለያዩ ጥቅሞችና ፍላጎቶች አሉ፡፡ ሁሉም ጥቅሙንና ፍላጎቱን በግል ለማስካት ከተንቀሳቀሰ ሰው እርስ በእርሱ መባላቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጥቅሞች በማሰባሰብ በማዋሃድ እና በማቀናጀት የግለሰቦች ጥቅሞች መዋቅራዊ ሜከ እንዲኖራቸው የሚያደርጉት ፓርቲዎች እና አባሎቻቸው ሁልጊዜ ማንፀባረቅ አለባቸው፡፡ ይህንን ለሞድረግ ለፓርቲ ዲሲፒሊን መገዛት የግድ ይላል፡፡ በሃገራችን ያሉ ተቃዋሚዎች እንኳን የህብረተሰቡን ጥቅም ሊያጣጥሙ የፓርቲዎቹ አመራሮች በሮህ ሳይቀር የሚስማሙ ናቸው፡፡ የትኛወንም የህብረተሰብ ጥቅም የሚወክል ፕሮግራም የላቸውም፡፡ ለብራል ርዕዮተ ዓለም እንከተላለን ቢሉን ለዚህ ፕሮግራሞች አልቀረፀም፡፡

## 4.ለህብረተሰቡ አማራጭ ማቅረብ

ፓርቲዎች ለምርጫ ከመወዳደራቸው በፊት የተጻፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በመነሳት መራጩ የተለያዩ ፕሮግራሞችንና አማራጮች በማገምገም የተሻለወን ለመምረጥ እድል ያገኛል፡፡ በሃገራችን አብዛኞቹ ተቃዋሚዎች የተጻፈ ፖሊሲና ፕሮግራም የላቸውም፡፡ ድምፁ ባገኙበት ቦታ ድምፁ ያገኙት በገዥው ፓርቲ የአፈፃፀም ችግሮች እንጂ በፕሮግራሞቻቸው አይደለም፡፡ አንዳንዴ በግል ፕሬስ ተብየው የሚሰጡትን አስተያየቶች እንደ ፕሮግራሞቻቸው ብንወስዳቸው እንኳ ለሚዳት በጣም አስቸጋሪ፣ እርስ በእርሳቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጋጩናቸው፡፡

## 5. የፖለቲካ ትምህርት ይሰጣሉ

በምርጫ ወቅት ፓርቲዎች የህብረተሰቡን ዋና ዋና ችግሮች ይዘረዝራሉ፡፡ ችግሮቹ የሚፍታቱን ስልቶችም እንዲሁ፡፡ ከስልቶቹ ሁሉ የትኛው የበለጠ ፍቱን መድኃኒት እንደሆነ በማሳየት የምርጫ ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን ሲያደርጉ የህዝቡ የፖለቲካ ንቃተ ህሊና እያደገ ይሄዳል፡፡ ለዳበረ ዴሞክራሲያዊ ባህል መሠረት ይጥላሉ፡፡ ህዝቡ የተለያዩ አማራጮችን በማገምገም ወደ ፓርላማ የሚገባወን አካል በምክንያታዊነት እንዲወስን ያደርጋሉ፡፡ ፓርቲዎችም ለዳበረ ዴሞክራሲያዊ ባህል መሠረት ይጥላሉ፡፡ በተለያዩ አማራጮች ላይ ፓርቲዎች በሚያካሂዱት ወይይት ለሀገር የሚበጀው ትክክለኛ ፖሊሲ የትኛው እንደሆነ መራጩ በካርዱ ይወስናል፡፡ የሃገራችን ተቃዋሚዎች ግን "ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም የምናነሳው ከምርጫ በኋላ ነው" ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሌለ ነገር ላይ ደምጻችሁን ስጡኝ ማለት ነው፡፡